የDCPS የPreK ቴክኖሎጂ፣ የተጠቃሚ መመሪያ

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

የPreK የቴክኖሎጂ የተጠቃሚ መመሪያ - ማውጫዎች

ክፍል (Section) 1: የዲቫይስ አጠቃላይ ምልከታ ... 2
ክፍል (Section) 2: አይፓድዎን (iPad) ማብራት እና መጠቀም ... 3
ክፍል (Section) 3: የአይፓድ (iPad) አቀማመጦች (Settings) እና ተግባራት ... 4
ክፍል (Section) 3: የአይፓድ (iPad) አቀማመጦች (Settings) እና ተግባራት ... 5
ክፍል (Section) 3: የአይፓድ (iPad) አቀማመጦች (Settings) እና ተግባራት ... 6
ክፍል (Section) 4: ኢንተርኔት (Internet) ማገናኘት ... 7
ክፍል (Section) 5: የአይፓድ (iPad)ን የመግቢያ ገጽ/ሆም ፔጅ (Homepage)ን መዳሰስ ... 8
ክፍል (Section) 6: የDCPS ካንቫስ (Canvas)ን ማግኘት ... 10
ክፍል (Section) 7: ማይክሮሶፍት ቲምስን (Microsoft Teams) ማግኘት ... 12
ክፍል (Section) 7: ማይክሮሶፍት ቲምስን (Microsoft Teams) ማግኘት ... 14
ክፍል (Section) 7: ክሌቨር (Clever) ማግኘት ... 16
ክፍል (Section) 8: የአይፓድ (iPad) የሽፋን ማቆሚያ (Case Stand) ... 19
ክፍል (Section) 8: ችግር መፍቻ (Troubleshooting) ... 20

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of Elementary Schools

DCPS Early Childhood
Start Early · Start Strong

ክፍል (Section) 1: የዲቫይስ አጠቃላይ ምልከታ

የPre-K ተማሪዎች፣ ከDCPS-የተሰጠ፣ '7th Generation 32GB Apple iPad'ን፣ በመኖሪያ ቤት የምናባዊ (virtual) ትምህርትን ለመከታተል ይጠቀማሉ። የECE የመማሪያ መድረኮችን (platforms) ለማግኘት እና ዲቫይሱን ለመጠቀም፤ በፍጥነት መጀመር የሚያስችለውን መመሪያ እባክዎን ይመልከቱ።



1 ፊት ለፊት የሚያይ (Front-facing) ካሜራ

2 ከላይ በኩል መጫኛ ቁልፍ (Top button)

3 የድምፅ መቆጣጠሪያ ቁልፎች (Volume buttons)

4 የሆም ቁልፍ/በጣት አሻራ መለያ (Home button/Touch ID)

5 የጀርባ ካሜራ (Rear camera)

6 የጆሮ ማዳመጫውን መሰኪያ (Headphone jack)

7 ወደኮምፒውተር ማገናኛ/ባትሪ ቻርጅ ማድረጊያ/የUSB ገመድ መሰኪያ (Lightning connector)

8 የSIM ማስቀመጫ (Wi-Fi + Cellular)

ክፍል (Section) 2: አይፓድዎን (iPad) ማብራት እና መጠቀም

እርምጃ 1: የተቆለፈ ስክሪን (lock screen) እስከምትመለከቱ ድረስ፣ ከላይ በኩል መጫኛ ቁልፉን (top button)፤ መጫን እና መልቀቅ – ወደ እርምጃ 2 መቀጠል። የተቆለፈ ስክሪን (lock screen) ካላያችሁ፣ የአፕል ምልክት (Apple icon) እስኪመጣ ድረስ፣ ከላይ በኩል መጫኛ ቁልፉን (top button)፣ መጫን እና መቆየት። አይፓዱ (iPad) ካልበራ፣ ምናልባት ባትሪውን ቻርጅ ማድረግ ያስፈልጋችሁ ይሆናል። የአይፓድ (iPad) ባትሪውን እንዴት ቻርጅ ማድረግ እንደሚቻል ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ የዚህን መመሪያ ክፍል (section) 3 እባክዎን ይመልከቱ።

እርምጃ 2: ሰዓቱን እና ቀኑን የሚያሳይ፣ የተቆለፈ ስክሪን (lock screen) ስትመለከቱ፣ አይፓዱን (iPad) ለመጠቀም፣ የሆም ቁልፉን (Home button) ይጫኑ።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of Elementary Schools

ክፍል (Section) 3: የአይፓድ (iPad) አቀማመጦች (Settings) እና ተግባራት

ማብሪያ እና የተቆለፈ (iPad) አይፓድን መክፈት

አይፓዱ (iPad)ን እየተጠቀማችሁበት ካልሆነ፣ የማሳያ (display) መስኮቱ፣ ባትሪውን ለመቆጠብ ሲል በራሱ ይጨልማል። አይፓዱን (iPad) እንደገና ለመጠቀም በምትፈልጉ ጊዜ፣ ፈጠን ብሎ ማስነሣት እና መጠቀም ይቻላል። አይፓዱን (iPad) ለማብራት፣ እባክዎን ከሚከተሉት አንዱን ያድርጉ:

1. ከላይ በኩል መጫኛ ቁልፉን (top button) ይጫኑ።



2. የሆም ቁልፉን (Home Button) በመጫንም፣ አይፓዱን ማብራት ይችላሉ።



DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS
Office of Elementary Schools

ክፍል (Section) 3: የአይፓድ (iPad) አቀማመጦች (Settings) እና ተግባራት

<u>ከአይፓዱ (iPad) ጋር መነጋገር</u>
አይፓዱን (iPad) እና በውስጡ ያሉትን አፕሊኬሽኖች (applications)፣ ቀላል የሆኑ ጥቂት እርምጃዎችን በመጠቀም፣ እንደ መታ ማድረግ (tap)፣ ጣትዎን ስክሪኑ ላይ እንደመጫር ማንቀሳቀስ (swipe)፣ ወደላይና ወደታች ማንቀሳቀስ (scroll)፣ እና አጉልቶ ማየት (zoom)፤ ያሉትን ጨምሮ መቆጣጠር ይችላሉ።

ታፕ (Tap): በአንድ ጣት በትንሹ ስክሪኑን መታ ማድረግ።

ስዊፕ (Swipe): አንድ ጣትን በስክሪኑ ወደጎን በኩል በፍጠነት ማንቀሳቀስ።

ስክሮል (Scroll): አንድ ጣትን በስክሪኑ ላይ ሳያነሱ ማስቀመጥ። በፍጥነት ለማንቀሳቀስ ወደታችና ወደላይ ማድረግ ወይም መንቀሳቀሱን ለማቆም ስክሪኑን መታ ማድረግ።

ዙም (Zoom): እርስ በርሳቸው የተቀራረቡ ሁለት ጣቶችን በስክሪኑ ላይ ማስቀመጥ። ጎላ አድርጎ (zoom in) ለማየት እነዚህን ጣቶች ማራራቅ እንዲሁም፤ ጣቶችን ወደእርስ በራሳቸው በማቀራረብ ደግሞ፣ ሰብሰብ ያለ እይታን (zoom out) እንድናገኝ ያደርጋል።

<u>በአይፓዱ (iPad) ላይ ድምፅን ማስተካከል</u>
ከአይፓዱ (iPad) ጎን የሚገኘውን የድምፅ ማስተካከያ ቁልፎችን በመጠቀም፤ የድምፅ አወጣጡን፣ የማስጠንቀቂያ ድምፆችን (alerts)፣ እና ሌላ ሚዲያን በአይፓዱ (iPad) ላይ ማስተካከል። ድምፁ እንዲጠፋ (mute ለማድረግ) የድምፅ መቀነሻ (volume down) ቁልፉን ተጭኖ እና ይዞ መቆየት።



DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS
Office of Elementary Schools

DCPS Early Childhood · Start Early · Start Strong

ክፍል (Section) 3: የአይፓድ (iPad) አቀማመጦች (Settings) እና ተግባራት

<u>በስክሪኑ ላይ ያለውን የታይፕ ማድረጊያ ቁልፎች (Keyboard) በመጠቀም፣ ጽሁፍን ማስገባት</u>

ጽሁፍን ለማረም (text editing) በሚፈቅዱ በማንኛውም አፕ (app) ላይ ሆናችሁ፣ ታይፕ የማድረጊያ ቁልፎች (keyboard)ን፣ በመፃፊያ ቦታው ላይ በመጫን ይክፈቱት። ጽሁፉን ታይፕ ለማድረግ የፊደል ቁልፎችን በመጫን ይቀጥሉ።

ጽሁፎችን በሚያስገቡ ጊዜ፣ ከሚከተሉት ማንኛውንም ማድረግ ይችላሉ:

- *በካፒታል ፊደሎች (uppercase letters) ታይፕ ለማድረግ:* 'Shift'ን ይጫኑ፣ ወይም 'Shift' ከነኩ በኋላ ወደ ፊደሉ ጣትዎን ያንሸራቱ።
- *የካፒታል ፊደል መቆለፊያ (Caps Lock)ን ማብራት:* የ'Shift' ቁልፉን ሁለት ጊዜ መታ መታ አድርጎ መጫን (Double-tap ማድረግ)።
- *ዓረፍተ ነገሩን በፍጥነት ለመጨረስና ነጥብ (period) እና ስፔስ (space) ማድረግ:* የስፔስ ባር (Space bar)ን ሁለት ጊዜ መታ መታ አድርጎ መጫን (Double-tap ማድረግ)።
- *ቁጥሮችን፣ ስርዓተ ነጥብን፣ ወይም ምልክቶችን ማስገባት:* የቁጥር ቁልፍን (.?123) ወይም የምልክት (symbol) ቁልፍን (#+=) ተጫኑ።
- *መጨረሻ ያደረጋችሁትን ለማስተካከል፣ እንደገና መቀልበስ (Undo ማድረግ): ይህን* ይጫኑ።
- *የአክሰንት ጭረት ያላቸውን ፊደላትን (accented letters) ወይም ሌላ አማራጭ ፊደላትን (characters) ማስገባት: ቁልፉን ተጭኖ መቆየት፣ ከዚያም የሚፈልጉትን አማራጭ ለመምረጥ ወደግራና ቀኝ መግፋት።*

- *በስክሪኑ ላይ ያለውን ታይፕ ማድረጊያ ቁልፍን (keyboard) እንዳይታይ ማድረግ: ታይፕ የማድረጊያ* (keyboard) ቁልፉን *መጫን።*

<u>የአይፓድ (iPad) ባትሪን ቻርጅ ማድረግ</u>

የአይፓድ (iPad) ባትሪያችሁን ቻርጅ ለማድረግ፣ ከአይፓዱ ጋር አብሮ በመጣው ገመድ እና የቻርጀር አዳፕተርን ተጠቅመው፣ በኤሌክትሪክ ማመንጫ ሶኬቱ ላይ መሰካት።



ክፍል (Section) 4: ኢንተርኔት (Internet) ማገናኘት

የሴሉላር አገናኝ በሆነ በቲ-ሞቢል (T-Mobile) አማካኝነት፣ አይፓዳችሁ (iPad)፣ ሁልጊዜ ወደ ኢንተርኔት እንደተገናኘ ይቆያል። ካስፈለገም፣ አይፓዳችሁን (iPad) ወደ ማንኛውም የምታገኙት የWi-Fi ኔትወርክ ማገናኘትም ትችላላችሁ። ወደ Wi-Fi ኔትወርክ ለማገናኘት፣ እባክዎን ከዚህ በታች የተመለከቱትን እርምጃዎች ይከተሉ።

1. ወደ አቀማመጦቹ (Settings) ይሂዱ፤ > ከዚያም ወደ Wi-Fi፣ ቀጥሎም Wi-Fiን ያብሩት (turn on ያድርጉ)።
2. ከሚከተሉት አንዱን ይጫኑ:
   - *ኔትወርክ (A network):* የሚስጥር ቁልፍ (password) ያስገቡ፤ የሚጠየቅ ከሆነ።
   - *ሌላ:* የማይታይ (hidden) ሌላ ኔትወርክን (network) መቀላቀል። የማይታየውን ኔትወርክ (hidden network) ስሙን፣ የጥበቃ ዓይነቱን (security type) እና የሚስጥር ቁልፉን (password) ያስገቡ።

ይህ ከእስክሪኑ በላይ በኩል ብቅ ካለ፣ አይፓዱ (iPad) ወደ Wi-Fi ኔትወርኩ ተገናኝቷል ማለት ነው። (ይህን ለማረጋገጥ፣ የድህረ-ገጽን (webpage) ለመመልከት፣ ሳፋሪን (Safari) የኢንተርኔት ማሰሻን (web browser) ይክፈቱ። የሳፋሪ የድህረ-ገጽ ማሰሻ (Safari web browser) ምልክት (icon) ይህንን ይመስላል:) ወደ እዛው ወደ ነበራችሁበት ቦታ ስትመለሱ፣ አይፓዱ (iPad) እንደገና ይገናኛል (reconnect ያደርጋል)።

<u>ሳፋሪ (Safari)ን በመጠቀም፣ ድህረ-ገጽን መዳሰስ (Browse ማድረግ)</u>

ኢንተርኔትን መጠቀም ለመጀመር፣ የሳፋሪን አፕሊኬሽን (Safari application)ን መክፈት። የድህረ-ገጽ አድራሻውን፣ በማሰሻው ከላይ በኩል በሚገኘው የአድራሻ ማስገቢያ ባር (bar) ውስጥ በማስገባት ድህረ-ገጹን መዳሰስ። በአይፓዱ (iPad) ላይ፣ ለጥቂት ጊዜያንት በመጫን፣ በቀላሉ ድህረ-ገጽን መዳሰስ ይችላሉ።

- *እንደገና ወደ ላይ ለመመለስ:* ወደታች ረጅም ከሆነ ገጽ፣ እንደገና ወደ ላይ በፍጥነት ለመመለስ፣ በስክሪኑ ከላይ በጠርዙ በኩል (top edge of the screen)፤ ሁለት ጊዜ መታ መታ አድርገው ይጫኑ (Double-tap ያድርጉ)።
- *የገጹን ተጨማሪ ክፍሉን በሰፋት ይመልከቱ:* አይፓዱን (iPad) ወደ ጎን በማዞር፣ ወደ 'landscape orientation' ማዞር።
- *ገጹን እንደገና ማደስ (Refresh ማድረግ):* ከአድራሻ መፈልጊያው አጠገብ የሚገኘውን፣ ይህን መጫን።
- *የድህረ-ገጹን፣ የዴስክቶፕ ስሪቱን (desktop version) መመልከት:* የሞባይል ስሪትን (mobile version) ሳይሆን፤ በምትኩ፣ የገጹን ሙሉ የዴስክቶፕ ስሪትን (desktop version) ለመመልከት፣ ይህን ይጫኑ እና፣ ቀጥለው ደግሞ 'Request Desktop Site' የሚለውን ይጫኑ።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of Elementary Schools

DCPS Early Childhood
Start Early · Start Strong

ክፍል (Section) 5: የአይፓድ (iPad)ን የመግቢያ ገጽ/ሆም ፔጅ (Homepage)ን መዳሰስ

የአይፓዱ (iPad) የሆም ስክሪን (home screen)፣ በዲቫይሱ ላይ የተጫኑትን ሁሉንም አፕሊኬሽኖች (applications) ወይም አፖች (apps) እንዲመለከቱ ያስችልዎታል። የPre-K ተማሪዎች፣ ሳፋሪ (Safari)፣ ካንቫስ (Canvas)፣ ማይክሮሶፍት ቲምስ (Microsoft Teams)፣ ሲሶ (Seesaw) እና ሃች (Hatch) ጨምሮ፤ ብዛት ያላቸውን አፖች (apps) ይጠቀማሉ።

1. ወደ ሆም ስክሪን (Home screen) ለመሄድ፣ ከስክሪኑ ከታች በኩል ወደላይ በጣትዎ ይጫኑ (swipe ያድርጉ) ወይም የሆም ቁልፉን (Home button) ይጫኑ።



2. በቀጣዮቹ የሆም ስክሪን ገጾች (Home screen pages) ውስጥ ያሉትን አፖችን (apps) ለመፈለግ፣ ወደግራ ወይም ወደቀኝ በጣትዎ መጫር (Swipe ማድረግ)።



3. አፕ (app)ን ለመክፈት፣ በሆም ስክሪን (Home screen) ያለውን ምስል (icon) ይጫኑ።

4. ወደ መጀመሪያው የሆም ስክሪን (Home screen) ገጽ ለመመለስ፣ ከስክሪኑ ከታች በኩል ወደ ላይ በጣትዎ ይጫሩ (swipe ያድርጉ) ወይም የሆም ቁልፉን (Home button) ይጫኑ።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of Elementary Schools

DCPS Early Childhood
Start Early · Start Strong

ክፍል (Section) 6: የDCPS ካንቫስ (Canvas)ን ማግኘት

የPre-K ተማሪዎች፣ የካንቫስ መድረክን (Canvas platform) ለምናባዊ (virtual) መማር ይጠቀማሉ። የኦንላይን የመማሪያ መቆጣጠሪያ ዘዴ የሆነውን፣ ካንቫስ (Canvas)ን፣ አስተማሪዎች እና ተማሪዎች የመማሪያ የመረጃ ምንጮችን (resources) ለማስተናገድ ይጠቀሙበታል። ካንቫስ (Canvas)ን፣ በ"Student" አፕ (app) አማካኝነት ማግኘት ይቻላል።

እርምጃ 1: የ"Student" አፕ (app) ላይ ይጫኑ።



እርምጃ 2. በ"Find my school"፣ በሚለውን ቁልፍ (button) ላይ ይጫኑ።

እርምጃ 3. የ"DC Public Schools" የሚለውን ታይፕ በማድረግ ይጀምሩ እና ከዚያም፤ በ"DC Public Schools (Students/Teacher/Staff)" የሚለው ሲመጣ፣ ይጫኑት።



Office of Elementary Schools

እርምጃ 4. የተማርውን የመጠቀሚያ ስም (username)፤ (ለምሳሌ፡ 12345678@students.k12.dc.us) ይጠቀሙ እና “Next” የሚለውን በመጫን ይግቡ (sign in ያድርጉ)። የሚስጥር ቁልፍ (password) እንዲያስገቡ ሲጠየቁ፣ የተማሪውን የአካውንት የሚስጥር ቁልፍ (password) ያስገቡ። የተማሪ የሚስጥር ቁልፍ (password)፣ የትውልድ ቀናቸው፣ በዚህ ‘MMDDYY’ አቀማመጥ ሲፃፍ ነው። ለምሳሌ፣ የትውልድ ቀንዎ፣ June 8, 2017 ከሆነ፣ የሚስጥር ቁልፍዎ (password) የሚሆነው፤ 060817 ይሆናል ማለት ነው።





ክፍል (Section) 7: ማይክሮሶፍት ቲምስን (Microsoft Teams) ማግኘት

ማይክሮሶፍት ቲምስ (Microsoft Teams)፣ የቪዲዮና የድምፅ ስብሰባዎችን በመጠቀም፤ በልጅዎ አስተማሪ የሚመራ፤ የቀጥታ ስርጭት፣ ዕለታዊ የክፍል ውስጥ ክፍለጊዜዎች ለማካሄድ ጥቅም ላይ ይውላል። ማክሮሶፍት ቲምስ (Microsoft Teams)ን ለማግኘት፣ እባክዎን ከዚህ በታች የተመለከተውን እርምጃዎች ይከተሉ።

እርምጃ 1: የ'Teams' አፕ (App.) ተጫኑ።

እርምጃ 2: የተማሪውን የመጠቀሚያ ስም (username)፤ (ለምሳሌ፡ 12345678@students.k12.dc.us) በመጠቀም ይግቡ (Sign in ያድርጉ)።



ክፍል (Section) 7: ማይክሮሶፍት ቲምስን (Microsoft Teams) ማግኘት

እርምጃ 3: የተማሪውን የአካውንት የሚስጥር ቁልፍ (password) ያስገቡ። የተማሪ የሚስጥር ቁልፍ (password)፣ የትውልድ ቀናቸው፣ በዚህ 'MMDDYY' አቀማመጥ ሲፃፍ ነው። ለምሳሌ፣ የትውልድ ቀንዎ፣ June 8, 2017 ከሆነ፣ የሚስጥር ቁልፍዎ (password) የሚሆነው፤ 060817 ይሆናል ማለት ነው።



እርምጃ 4: በ“Teams would like to Send You Notifications” በሚለው መልዕክት ላይ፣ “Allow” የሚለውን ይጫኑ።



DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of Elementary Schools

DCPS Early Childhood
Start Early · Start Strong

እርምጃ 5: እባክዎን፣ “Teams would like to access the Microphone” የሚለው መልዕክት ሲመጣ፣ “OK” የሚለውን ይጫኑ።



DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of Elementary Schools

DCPS Early Childhood
Start Early · Start Strong

ክፍል (Section) 7: ክሌቨር (Clever) ማግኘት

ክሌቨር (Clever) ተማሪዎች የተለያዩ በርካታ የትምህርት አፕሊኬሽኖችን (applications) ማግኘት የሚችሉበት፣ ጥበቃ የተሰጠው (secure) ፖርታል ነው። ከዚህ በታች የተሰጡትን፣ የክሌቨር አፕስ (Clever apps) እርምጃዎችን እባክዎን ይከተሉ።

እርምጃ 1: የክሌቨርን አፕ (Clever app) ይጫኑ።

እርምጃ 2: “Scan Clever Badge” የሚለውን፣ ካሜራውን የሚያሰራውን ስክሪን ያዩታል። ካሜራውን ለማግኘት ፍቃድ መስጠት የሚፈልጉ ከሆነ፤ “Allow” የሚለውን መጫን አለብዎት ። አሁን፣ የተማሪውን የክሌቨር ባጅ (Clever badge)፤ ከትምህርት ቤትዎ ተሰጥቶት ከሆነ፤ ስካን (Scan) ያድርጉ። ባጅ (badge) ካልተሰጠው፣ “Log in with username/password”፣ የሚለው ላይ ይጫኑ።

በ“Log in with username/password” ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጫኑ፣ ይህ መልዕክት መጥቶ፤ “Search for your school” የትምህርት ቤትዎን ስም እንዲፈልጉ ይጠየቃሉ። እባክዎን የትምህርት ቤት ስሙን ታይፕ ያድርጉ፤ ወደታች የሚዘረዘረው (drop-down list) ላይ አፑ (app) ጥቂት አማራጮችን ያስቀምጥልዎታል። ትክክለኛውን ትምህርት ቤት ይምረጡ። ትምህርት ቤትዎን ከመረጡ በኋላ፣ ወደ መግቢያ (login) ገጹ ቀይሮ ይመራዎታል። የ“Student and Staff login with office365” የሚለውን ይምረጡ።



እርምጃ 3: የተማርውን የመጠቀሚያ ስም (username)፤ (ለምሳሌ፡ 12345678@students.k12.dc.us) ይጠቀሙ እና “Next” የሚለውን በመጫን ወደ መግቢያው (sign in) ይሂዱ። የሚስጥር ቁልፍ (password) እንዲያስገቡ ሲጠየቁ፣ የተማሪውን የአካውንት የሚስጥር ቁልፍ (password) ያስገቡ። የተማሪ የሚስጥር ቁልፍ (password)፣ የትውልድ ቀናቸው፣ በዚህ ‘MMDDYY’ አቀማመጥ ሲፃፍ ነው። ለምሳሌ፣ የትውልድ ቀንዎ፣ June 8, 2017 ከሆነ፣ የሚስጥር ቁልፍዎ (password) የሚሆነው፤ 060817 ይሆናል ማለት ነው።





እርምጃ 4: የክሌቨር ፓርታልን (Clever portal) መፈለግ (Browse ማድረግ)።



ክፍል (Section) 8: የአይፓድ (iPad) የሽፋኑ ማቆሚያ (Case Stand)

ከDCPS-የተሰራጩ አይፓዶች (iPads) ከጉዳት መጠበቂያ ሽፋኖች (protective cases) አብረው ተከተው የተላኩ ሲሆን፣ ይህም እንደ የአይፓዱ (iPad) የድጋፍ ማቆሚያ ሆኖም ያገለግላል። አይፓድዎን (iPad) ደግፎ ማቆሚያውን በሚገባ ለመጠቀም፤ በስዕሉ ላይ ከታች እንደሚታየው በትናንሽ መቆንጠጫ መሰል ማስገቢያው ውስጥ፣ ከጉዳት የመጠበቂያ ሽፋኑ ማዕዘናት መግባቱን ያረጋግጡ።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of Elementary Schools

DCPS Early Childhood
Start Early · Start Strong

ክፍል (Section) 8: ችግር መፍቻ (Troubleshooting)

በተማሪው መግቢያ (logins)/የሚስጥር ቁልፎች (passwords) ወይም የመማሪያ መድረኮችን (ማለትም፤ ካንቫስ (Canvas)፣ ቲምስ (Teams) ያሉትን)፣ ፈልጎ ከማግኘት ጋር የተያያዙ፣ ሌላ ቴክኒካል ችግሮችን ወይም ከDCPS-የተሰጠ ዲቫይስ ላይ እርዳታን ካስፈለጋችሁ፤ የአስቸኳይ ጊዜ መስመሩን (hotline) በ**202-442-5885** በመደወል እርዳታን መጠየቅ ይችላሉ። የቴክኒካል እርዳታው 24/7 የሚገኝ ሲሆን፣ ይህ የሆነበት ምክንያት፣ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ፤ በመኖሪያ ቤት ውስጥ መማር፣ የተለየ ተሞክሮ እንደሆነ ስለምናውቅ ነው። ለተጨማሪ ችግር መፍቻ (troubleshooting) እርዳታ ለማግኘት፣ backtoschool.dc.gov ይጎብኙ።

ስለ ካንቫስ (Canvas) ጥያቄዎች ካለዎት፣ ትምህርት ቤትዎን ማነጋገር ይችላሉ።

24/7 የቴክ አገልግሎት ለቤተሰቦች

በተማሪው፤ መግቢያ (logins)/የሚስጥር ቁልፎች (passwords)፣ ካንቫስ (Canvas) ወይም ቲምስ (Teams)ን ለማግኘት ስለተቸገሩ፣ ወይም ከDCPS ዲቫይስዎ ጋር ችግሮች ስለገጠመዎ እርዳታ ይፈልጋሉ?

ደውሉልን! (202) 442-5885